ዶን ፍሌሚንግ / Don Fleming

# መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ ይናገር

ፔንታ-ጌትስ ሆሊቲክ ጎስፕል ምኒስትሪ
Pent-gets Holistic Gospel Ministry
Addis Ababa (Ethiopia)
1999/2007

ተርጓሚ ኀይሉ ልመንህ
ዋና አርታዒ መሐሪ ፈንታ

ይህ መጽሐፍ የተተረጐመው
"Let the Bible Speak for Itself"
**Don Fleming**

**Bridgeway Publications**
**GPO Box 2547**
**Brisbane 4001**
**Australia**
**Printing in Australia by McPherson's printing group**
ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን፥ የታተመውም በደራሲው ፈቃድ ነው::

በፔንታ-ጌትስ ሆሊስቲክ ጎስፐል ምኒስትሪ
ተተርጐሞና ተዘጋጅቶ ታተመ
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

**Publisher**
Penta-gets Holistic Gospel Ministry
Addis Ababa (Ethiopia)
1999 / 2007

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው / ALL RIGHTS RESERVED

# ማሳሰቢያ

ከኅትመት በፊት አርታዕያን፥ የመጽሐፉን ትርጉም በሙሉም ሆነ በከፊል አንብበው አርትዖታቸውን ለግሠውናል፤ የሰጡን አርትዖትም የተዛባውን በማስተካከል ደረጃ ጠቅሞናልናል፤ ስለዚህም ልዑል እግዚአብሔር ይባርካቸው እንላለን:: አብዛኛዎቹ አስተያየቶቻቸው በኅትመቱ ውስጥ ተካትተዋል:: አምስቱ ግን ሳይለወጡ እንዲታተሙ ተደርገዋል:: ለምን ይህን እንዳደረግን ለአርታዕያኑ፥ እንዲሁም ለመሰል አንባብያን መግለጽ ካስፈለገ ምክንያቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል::

## 1. ድርብ ሠረዝ (፤) : -

«ልጆችን ወለድሁ፤ አሳደግኋቸውም፤
እነርሱ ግን ዐመፁብኝ»፤ (ኢሳ. 1፥2)::

ከዐረፍተ ነገሩ ቀጥሎ አራት ነጥብ (::) መደረግ አለበት የሚል ሐሳብ ቀርቦ ነበር፤ ሆኖም ከጥቅሱ በኋላ የሚቀመጥ ሌላ ሥርዐተ ነጥብ ለጊዜው ስለሌለን ድርብ ሠረዝና አራት ነጥብ በዚህ መልኩ በአገልግሎት ላይ ውለዋል::

## 2. አጽንዖት / አጽንኦት : -

- ❖ አጽንኦት «አጽንአ» ☛ አጠና፤ አፀና፤ አጠነከረ፤»
  ከሚለው የግዕዝ ግሥ የወጣ ሲሆን፥

- ❖ አጽንዖት ደግሞ «ጸንዐ» ☛ ጸና»
  ከሚለው ሌላ የግዕዝ ቃል የወጣ ነው::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አጽንዖት ለተባለው ቃል (ኦ) የተባለው ፊደል ቢገባ በቋንቋው ባለቤቶች ዘንድ የትርጉም ለውጥ በማምጣት ግርታን ይፈጥራል፤ በመሆኑም ይህን መጽሐፍ ሲያነቡት የሚያስከትለውን የትርጉም ለውጥ ለመከላከል «<u>አጽንዖት</u>» ለተባለው ቃል (ዖ) የተሰኘው ፊደል ገብቷል::

3. ኀ ÷ ኃ : -

«ኀጢአት» ፥ «ኀይል» በተሰኙት ቃላት ውስጥ «ኀ» ወደ «ኃ» ሊለወጥ እንደሚገባ ሐሳብ ቀርቦበት ነበር። ሆኖም በተጠቀሱት ቃላት ውስጥ የ4ኛው ፊደል »ኃ» ሳይሆን የመጀመሪያው ፊደል (ግዕዙ) «ኀ» ተጽፏል፤ ስህተትም አይደለም።

4. አናባቢ ቃላት : -

ራሱን የቻለ ትርጉም ካለው ቃል ጋር የሚገኙ አናባቢ ቃላት ሁሉ በስሕተት የታሰፉ ካልሆኑ በቀር ለየብቻ ቆመዋል፤ ራሱን የቻለ ትርጉም ከሌለው ቃል ጋር ከሆኑ ግን ከተከታዩ ቃል ጋር በተለጣፊነት ቆመዋል። ለምሳሌ : -

- ➩ «ስለሚመጣ» «ስለ መጣ»፥
- ➩ «እስከሚሆን» «እስከ ሆነ»፥
- ➩ «እንደሚቀጥለው» «እንደ ቀጠለ»

ከ «ሚመጣ፥ ሚሆን፥ ሚቀጥለው» ጋር ያሉት አናባቢ ቃላት ተለጣፊ ሆነው ሲገቡ «መጣ፤ ሆነ፤ ቀጠለ» ከተሰኙት ቃላት ጋር የተጣመሩት ግን ለየብቻ ቆመዋል። በነዚህ ምሳሌዎች ሁሉንም ማየት ይቻላል።

5. ድነት / ደኅንነት

- ➩ «ደኅንነት» ☛ ድኅነ ☛ ዳነ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን
- ➩ «ድነት» ደግሞ «ዳነ» ከሚለው የአማርኛ ቃል የወጣ ነው።

ቃሉ በአዲሱ መደበኛ ትርጉም (መጽሐፍ ቅዱስ) እርትዖት ጊዜ አነጋገር ነበር። በኋላ ግን «ድነት» የተሰኘው ቃል «ደኅንነት» የተሰኘውን የግዕዝ ቃል እንዲተካ ስለ ተወሰነ «ደኅንነት» የሚለው ቃል እየ ተለወጠ «ድነት» የሚለው ቃል ተተካ። በዚህ መጽሐፍም በ«ደኅንነት» ፈንታ «ድነት» የሚለው ቃል ገብቷል፤ የትርጉም ለውጥም አያመጣም። ሆኖም የዚህ ጽሑፍ እርትዖት እንከን የማይገኝለት ነው የሚል ትምክህት የለንም፤ በዚያ ፈንታ የመጽሐፉ ተጠቃሚዎች ምጽሐፉን አንብበው የሚሰጡንን ትክክለኛ ማስተካከያ የማንቀበልበት ምክንያት አይኖርም።

መሐሪ ፈንታ (አርታዒ)

# የፔንታ-ጌትስ ሆሊስቲክ ጎስፐል ምኒስትሪ

**(ሀ) አድራሻ : -**

**ፔንታ - ጌትስ ሆሊስቲክ ጎስፐል ምኒስትሪ /ፔሆጎም/**

Pent-gets Holistic Gospel Ministry /PHGM/

**መ. ሣ. ቁ. / P. O. BOX 5767**

**አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ /** ADDIS ABABA, THIOPIA

**(ለ) አርማ : -**

**(ሐ) ትርጉም : -**

ለቃሉ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር «ፔንታ ጌትስ ሆሊስቲክ ጎስፐል ምኒስትሪ» ማለት በአምስቱም የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ዋና በሮችና አገር አቋራጭ መንገዶች በመውጣትና በቅርብ ርቀት በመጓዝ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰዎች ሰማያዊና ምድራዊ ሕይወት የሚናገረውን ሳይለውጥ፥ ሳይጨምርና ሳይቀንስ በገጠርና በከተማ ለሚኖሩ ሰዎች በመስበክ፥ በማስተማር፥ ሥልጠና በመስጠት ወደ አምስቱም የኢትዮጵያ ጠረፎችና አዋሳኝ ሀገሮች የሚገሠግስና ከዚያም ሊያልፍ የሚችል የወንጌል አገልግሎት ማለት ነው።

# መጽሐፉን መተርጐም ያስፈለገበት ምክንያት

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው የነገደ ኩሽና የነገደ ሳባ አረማዊ የአምልኮ መንፈስ፥ እንዲሁም የይሁዶ አክራሪ መንፈስ ሥር በሰደዱበት ዘመን ነው። እነዚህ ተግዳሮቶች ክርስትና ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባና ከገባ በኋላም ሥር ሰዶ እንዳያድግ ደንቃራ ሆነውበት ቆይተዋል። በኋላ የገጠሙት ተግዳሮቶች ደግሞ የክርስቶስን አምላክነት በገሐድ ከሚቃወመው መንፈስ ሌላ በራሱ በክርስትናው ውስጥ ተወልደው እያደጉ ያሉት የስሕተት ትምህርቶች ናቸው።

እነዚህ የስሕተት ትምህርቶች አንዳንድ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ካለመረዳት የሚመነጩ ሲሆኑ፥ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለራስ ጥቅም ታስቦ በሚሰበክ ሰብአዊ አስተሳሰብ የተነሣ የሚፈጠሩ ናቸው። የቤተ ክርስቲያን ብርታቷም ከአገልጋዮቿ ብርታት የተነሣ ሲሆን ውድቀቷም ከአገልጋዮቿ ድክመት የተነሣ መሆኑ የማይካድ ነው። አግልጋዮቿ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል በመተርጐምና በማብራራት የሕዝቡን ልብ ወደ እውነት የመመለስ ችሎታ ካላቸው ቤተ ክርስቲያንን ከክህደት ማዕበል ይታደጓታል። አነርሱ ደካሞች ከሆኑ እንዲሁም በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚጨምሩ፥ ከቃሉ፥ የሚቀንሱ ወይም ቃሉን የሚለውጡ ከሆኑ ተከታዮቻቸውም እንዲሁ ይሆናሉ። በመጨረሻም በእግዚአብሔር ቃል ላይ ወንጀል የሚፈጽሙ ሁሉ ከቅጣት አያመልጡም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል፦

«እኔ ያዘዝኋችሁን የአምላካችሁን፣ የእግዚአበሔርን ትእዛዝ ትጠብቃላችሁ እንጂ ባዘዝኋችሁ ቃል ላይ አትጨምሩም፤ ከእርሱም አታጉድሉም»፤ (ዘዳግም 4፥2)።

«እኔ የማዝዝህን ነገር ሁሉ ታደርገው ዘንድ ጠብቅ፤ ምንም በእርሱ ላይ አትጨምር፤ ከእርሱም ምንም አታጉድል»፤ (ዘዳግም 12፥2)።

«. . . እንዳይዘልፍህ፣ ሐሰተኛም እንዳትሆን በቃሉ ላይ አንዳች አትጨምር»፤ (ምሳሌ 30 (6)፥5-6)።

«በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የተንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሰፍቶች ይጨምርበታል፤ ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች

እንዳች ቢያጕድል በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን የጕድልበታል፤ (ራእይ 22፥8-19):: እነዚህና መሰል ጥቅሶች ሁሉ ቃሉን እንዳንሸቃቅጥ ያስጠነቅቃሉ::

«መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ ይናገር» የተሰኘው መጽሐፍ ክቡርና ሙሉ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚጨምሩትን፥ ከእርሱም የሚያጕድሉትን፥ ወይም ቃሉን የሚለውጡትን ሰዎች የሚገድብበት ልጓም አለው:: ሰባክያንና መምህራን እንደዚሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሪዎችና በግላቸው መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ቃሉን ለማገልገል በመለማመድ ላይ ያሉ ሁሉ፥ ከዚህ አዳጋ የሚያመልጡበትን ጥበብ ያመለክታል:: ሰባክያንና መምህራን በራሳቸው ጥረት ሰዎችን ለመለወጥ የሚያደርጉትን ጥረት ቆም አድርገው ወይም ትተው መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል በማብራራትና በማስተማር ብቻ፥ እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚያመጣውን ለውጥ እንዲጠብቁ ይመክራል::

መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ተራወይም የታሪክ መጽሐፍ አድርገን እንዳናነበው፥ ለመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ምን ማለቱ እንደ ሆነ፥ በማጤን እንድንቀበለው፥ ስለ ክርስትናና ስለ መንፈሳዊ ሕይወታችን ብቻ ሳይሆን ስለ ዕለታዊ ኑሯችንም የሚሰጠን ትምህርት በማጥናት እንድነታዘዘው ያስተምረናል::

መጽሐፍ ቅዱስን ከማያምኑ ሰዎች ጋር ማጥናት የምንችልበትን ስልት ያመለክተናል:: ምንም ዐይነት አበቃ የምንለው፥ ከፍጻሜ የሚደርስ ጥናት የለም ይልና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችንን ቸል እንዳንል የማንቂያ ደወል በመደወል ለማንበብ፥ ለማጥናትና ለማገልገል ያነቃናል::

መጽሐፉ በእነዚህና በመሰል ምክንያቶች ከአገልግሎታችን ዐላማ ጋር ስለሚስማማ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችና ሰባክያን ለሆኑ፥ እንደዚሁም መጽሐፍ ቅዱስን በግላቸው በማጥናት ለሚያገለግሉ ሁሉ ጠቃሚ ሆኖ ስለ አገኘነው አጋዥ የማሠልጠኛ መጽሐፍ አድርገን ልንጠቀምበት ፈለግን:: ስለዚህም ከእንግሊዝኛው ጽሑፍ ወደ አማርኛ መልሰን አሳተምነው፤ እርስዎም ይጠቀሙበት::

**ፔንታ - ጌትስ ሆሊስቲክ ጎስፐል ምኒስትሪ**

# ምስጋና

1. ይህን መጽሐፍ አስተርጉመን እንድናሳትም አነሣስቶ ላስጀመረንና ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባው! አሜን!

2. መጽሐፉን አስተርጉመን እንድናሳትም የፈቀዱልንና የረዱንን ደራሲውን ዶን ፍሌሚንግንና ባለቤታቸውን ጌይ ፍሌሚንግን ልዑል እግዚአብሔር ከመላ ቤተ ሰባቸው ጋር ይባርካቸው።

3. መጽሐፉን በሙሉም ሆነ በከፊል በማንበብ በአርትዖት ላገዙን ወገኖች፥ ለወንድም :- ዳንኤል ታደሰ፥ ስለሺ ፍትሐ-እምላክ፥ ቴዎድሮስ ግዛው፥ መምህር ወልደ ሐዋርያት ሳሙኤልና ለወ/ሮ ፍቅር አዲስ ሙሉ የልዑል እግዚአበሔር ጸጋ ይብዛላቸው።

4. መጽሐፉን በሚገባ አንብበው ተመሳሳይ አርትዖታቸውንና በሽፋኑ ላይ የሚታተሙ ሐሳቦቻቸውን የሰጡንን አለቃ ቤተ-መንግሥት ቤተ-ክህነትን ወንድም ምኒልክ አስፋውን፥ መምህር በልሁ ደሰለኝን፥ መምህር ዐይናለም ሣይማኖትን፥ መጋቢ አበጀሁ ዳመነን፥ መጋቢ ስሜ ታደሰን ወንድም ሚካኤል ዘወደን ልዑል እግዚአብሔር ከማያልቀው በረከቱ ይባርካቸው፤ አሜን።

## መውጫ

**አርእስት** **ገጽ**

❖ መግቢያ ........................ 10
፩. ትክክለኛው የማጥኛ መንገድ ........ 12
፪. በማስተዋል ማንበብ (1) ........ 19
፫. በማስተዋል ማንበብ (2) ........ 29
፬. ሌሎችን መርዳት........ 39
፭. የስብከት አዘገጃጀት ........ 46
፮. ተቀባዩን ዒላማ ያደረገ ስብከት........ 58
፯. ይዘቱን መቈጣጠር........ 68
፰. ብሉይ ኪዳንን ማብራራት (1) ........ 74
፱. ብሉይ ኪዳንን ማብራራት (2) ........ 83
፲. አዲስ ኪዳንን ማብራራት (1) ........ 94
፲፩. አዲስ ኪዳንን ማብራራት (2) ........ 101
፲፪. የትምህርቱን መረሐ ግብር ማዘጋጀት........ 110
፲፫. ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችን ስለ ማስተማር........ 121
፲፬. እያሻሻሉ መራመድ........ 134
❖ በደራሲው ተዘጋጅተው የታተሙ መጻሕፍት
(Books by the same author) ........ 139

ደግሞ አድማጩን ከግምት ውስጥ ያላስገባ፥ ያልተጨበጠ ትምህርት ነው። ይሁን እንጂ ሌላ መካከለኛ መንገድ አለ፤ ይህ መጽሐፍም የሚያስተምረው ይህንኑ ነው።

የእኔም ዓላማ እኛ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች የሆንን በየጥናቱ መድረክ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ማብራራት እንደምንችልና፥ በዚህም ወቅት የአድማጩን የምገባ ፍላጎት ሳንዘነጋ ቀጥተኛውን ተግባር በሥራ ላይ ማዋል እንዳለብን ዘዴውን ማቅረብ ነው። ስብከታችንን የሚያዳምጡትን ምእመናን ውስብስብ በሆነ አስቸጋሪ ሐሳብ ሳናደክማቸው፥ የምናስተምረውን ጥቅስ ከመልእክቱ ትርጉም ሳንወጣ መግለጽ ይጠበቅብናል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ርእሰ ጉዳዮች ቀደም ሲል ከዐሥራ ሁለት በላይ በሚሆኑ አገሮች ለትምህርት የቀረቡ ናቸው። እነዚህ የትምህርት ርእሶች ባብዛኛው የተውጣጡት «በሪጅ ሀንድ ቡክስ» በሚል ርእስ ካዘጋጀኋቸው 8 ተከታታይ መጻሕፍት ውስጥ ነው። እነዚህን ለትምህርት የቀረቡ ምንባቦች ማብራሪያቸውን በታይፕ አዘጋጅቼ ሰባክያን ለሚያዘጋጇቸው ስብከቶች መሠረት ይሆኗቸው ዘንድ በታላቅ ደስታ አበረከትሁ።

በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ አንባቢዎች ሥራው በሚገባ ተሠርቶላቸው አያገኙትም፤ ስለዚህ ለራሳችንም ሆነ ለአድማጮች ማድረግ ያለብን የበኩላችንን ጥናት ማካሄድና ስለ አተገባበሩ ማሰብ፥ ከዚያም ልምምዱ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል ማዕከል ያደርግ ዘንድ አስተዋጽኦ ማበርከት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን ከሕይወታችን ጋር የሚያገናኝበት የራሱ የሆነ መንገድ አለው፤ ብዙ ጊዜ ይህን ማድረግ የሚችለው በእኛ ዘንድ ግንዛቤን ሲያገኝ ብቻ ነው። አንባቢዎች መጽሐፍ ቅዱስን ደኅና አደርገው በማወቅ፥ ለመስበክና ለማስተማር እንዲበቁ፥ በዚያውም የሌሎችን መንፈስ ለቃሉ ለመቀስቀስ እንዲችሉ፥ ይህ መጽሐፍ አጋዥ ኀይል እንዲሆንላቸው ጸሎቴ ነው።

ዶን ፍሌሚንግ

## ፩

# ትክክለኛው የማጥኛ መንገድ

## ልዩ መጽሐፍ፥ ግን ደግሞ ቀላል

መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ፥ የምናነበው መጽሐፍ ተራ መጽሐፍ አለመሆኑን ወዲያውኑ እንገነዘባለን። ክርስቲያኖች ከሆንን መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል፥ ስለ እግዚአብሔር ማንነት የሚያሳውቀን፥ እግዚአብሔር ለፈጠረው ሕዝብ ምን ምን ተግባራትን እንደ ፈጸመ የሚያስገነዝበን መጽሐፍ መሆኑን ዐውቀን እናነበዋለን። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ከእግዚአብሔርና ከእርስ በርሳቸው ጋር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያስተምረናል።

እግዚአብሔር በህልውናው ዘላለማዊ ነው፥ ስለሆነም ማንነቱንና ባሕርዩን በቁሳዊው ዓለም ውስጥ በምናያቸው ነገሮች ልንመዝነው አንችልም። ሰብአዊ አካል የሌለውን፥ ለዕውቀቱና ለጥበቡ ድንበር የማይደረግለትን፥ ዘላለማዊ ባሕርይ ያለውን አምላክ ሰብአዊ መግለጫ አጥጋቢ ሆኖ ሊገልጸው ከቶ አይችልም። እንዲህ ሲባልም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከእኛ ግንዛቤ በላይ ነው ማለትም አይደለም። እግዚአብሔር ውስን የሆነው ዓለም ከሚገልጸው በላይ ታላቅ ቢሆንም፥ ውስን በሆነው ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ በብዙም ሆነ በጥቂቱ ያውቁታል። ታዳጊ ልጆች ወላጆቻቸውን የሚያሳስበውን ግላዊም ሆነ ማኅበራዊ ተግባር አይገነዘቡትም፤ ሆኖም ከወላጆቻቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት ደስተኞች ናቸው። ወላጆቻቸውም ከልጆቻቸው ጋር ኅብረት ያደርጋሉ። እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ስናጠነክር ራሱ ይናገረናል፤ እንድንገነዘበውም ይረዳናል።

ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ከመጻሕፍት ሁሉ በላይ የላቀ መጽሐፍ፥ የእግዚአብሔር ቃል፥ ነው፤ አስቸጋሪ መጽሐፍም አይደለም። እግዚአብሔር ሲናገር፥ ማንኛውም ሰው በሚገባው መንገድ ይናገራል። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳይገነዘቡት ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ ይህን ሐቅ አለማጤናቸው ነው። እነርሱ እንደሚገምቱት አንድ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን፣ ራሱ ከመሰከረ፥ ትርጉሙ ጥልቅ ስለ ሆነ፥ ሰዎች ሊገባቸው አይችልም ይላሉ። እንዲያውም አንዳንዶቹ መጽሐፍ ቅዱስ መልእክቱን ቀላል በሆነ ቋንቋ ካቀረበ ክብሩ እንደ ጎደለ ይቈጥሩታል።

መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ የሚያቀርባቸውን ታላላቅ እውነቶችና እነዚህን እውነቶች እንዴት እንደሚገልጻቸው ደኅና አድርገን ማስተዋል አለብን። ምናልባት ሰብአዊ አዕምሯችን የተገለጠውን እውነት ሙሉ ትርጉሙን በሚገባ ለመገንዘብ ዐቅም ላይኖረው ይችላል፤ (ለምሳሌ ዘላለማዊውና ያልተፈጠረው

የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ፥ ከእግዚአብሔር ፍጥረታት እንደ አንዱ ሆኖ በዚህ ዓለም ውስጥ ተወለደ)፤ ይህ ሁኔታ ስለተገለጠው እውነት እንዳናውቅ ዕንቅፋት ሊሆንብን አይችልም፤ (ይህ የተገለጠው እውነት የኢየሱስ ልደት ነው):: በተመሳሳይ መንገድ ቅዱስና ጻድቅ የሆነው አምላክ እንዴት አድርጎ ኀጢአተኞችን በማጽደቅ ወደ እርሱ እንደሚቀበላቸው ምሥጢሩን ልንገነዘብ አንችልም የሚል ስሜት አለብን፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ግን ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ትክክል፥ የማያወላውልና ሊገባም የሚችል እውነት ነው:: (ማለትም የኢየሱስ ሞት እግዚአብሔር ይህን እንዲፈጽም አስችሎታል)::

ብዙ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነቡበት ጊዜ ለመረዳት ከባድ መጽሐፍ መሆን አለበት የሚለው አስተሳሰባቸው ትልቁ ችግራቸው ነው:: እንዲያውም በቀላሉ የሚገባቸው ከሆነ መንፈሳዊ ስሜታቸውን የሚቀንስ መስሎ የሚታያቸው ከመሆኑም በላይ እንደ እግዚአብሔር ቃል አይቈጥሩትም:: ይህ ዐይነቱ አመለካከት ያላቸው አንባብያኑ ብቻ ሳይሆኑ ሰባክያኑም ጭምር ናቸው:: አብዛኛውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ለግንዛቤ ከባድ የሚሆነው ሰባክያኑ እንዲህ እንዲሆን ስለሚያደርጉት ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ፥ መንፈሳዊነታቸውን፥ አልያም የተማሩ መሆናቸውን ሰዎች እንዲያደንቁላቸው ስለሚፈልጉ ነው:: ይሁን እንጂ ከዚህ ይልቅ አድማጮቻቸው በፊት ከነበሩበት ሁኔታ ተላቀው አሁን ከመድረኩ ባገኙት ትምህርት አማካይነት መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ ተረድተውና መንፈሳቸው ረክቶ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

## ማንኛውም ሰው ሊገነዘበው ይችላል

መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ የሚያደርገው አስደናቂው ነገር አያሌ ምሁራንና ሊቃውንት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መታወቅ የሚገባውን ሁሉ ማወቅ ሲሳናቸው፥ በአንጻሩ ያልተማሩ ሰዎች ሊገነዘቡት መቻላቸው ነው:: ጥንት ቅዱሳት መጻሕፍት በተጻፉበት ጊዜ የነበሩት የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች፥ ዛሬ በከፍተኛ ደረጃ ከተማሩት ሰዎች ጋር ሲመዛዘኑ በትምህርት ደረጃቸው ከፍተኛ እንዳልነበሩ ልናስታውስ ይገባናል:: እንዲያውም የአዲስ ኪዳን መልእክተኞች የተላኩላቸው አብዛኛዎቹ ሰዎች ከዚያ በፊት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ትውውቅ የሌላቸው ነበሩ:: ይሁን እንጂ እነዚያ ሰዎች የተጻፏትን መልእክቶች ሐሳብ ይገነዘቡ ነበር::

ዛሬም አንዳንድ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳይገነዘቡት ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ ከማንበባቸው የተነሣ ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ ሰባክያኑ በተሳሳተ ሁኔታ በመስበክ ተመሳሳይ ስሕተትን ስለሚፈጽሙ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስን በተሻለ ሁኔታ ለማወቅ እንደ አንባብያንም፥ እንደ ሰባክያንም ለረጅም ጊዜ ተተክሎ የቆየውን አጕል ልማድ መለወጥ ያስፈልገናል::

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት የእግዚአብሔር መንፈስ ባደረባቸው ሰዎች እንደ ሆነ ክርስቲያኖች ያምናሉ፤ (2ጴጥ. 1፥21)። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የዘመኑ ቴክኖሎጂ እንደ ፈጠረው፥ ሰውን ተክቶ እንደሚሠራ ሮቦት አልነበሩም። እግዚአብሔር መልእክቱን እንደ ፈለገ የሚያስተላልፍባቸው የጽሕፈት መኪናም አልነበሩም። ጸሐፊዎቹ አስተዋዮችና አዋቂዎች ከመሆናቸውም በላይ፥ መጻሕፍቱን ሲጽፉ የሚያስተላልፏቸው መልእክቶች ነበሯቸው። ይህን ያደረጉት በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ስለ ነበር ቅዱሳት መጻሕፍቱ የእግዚአብሔር ማኅተምና ይሁንታ በውስጣቸው ይታያል፤ በመሆኑም ለማስተማር፥ ለመገሠጽ፥ ለማቅናት፥ በጽድቅም መንገድ ለመምከር ሥልጣኑ አላቸው፤ (2ጢሞ. 3፥16-17)።

ጳውሎስ መልእክቱን ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ፥ ክርስቲያኖች በውስጣቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ስላላቸው እግዚአብሔርንና ዕቅዱን የማወቅ ብቃት አላቸው ብሏል፤ (1ቆሮ. 2፥10-13)። እንዲህ ሲባልሞ ክርስቲያኖች ከሆንን በኋላ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ አያስፈልገንም ማለት አይደለም። በአንጻሩ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ለእኛ የሰጠበት ምክንያት፥ በውስጣችን ያደረው መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን የሚፈጽመው ተግባር፥ የሚያከናውነው ታሪክና ሥራ መኖሩን በትምህርቱ አማካይነት ለመግለጽ፥ መጽሐፍ ቅዱስ መጠናት እንደሌለበት ለማሳየት ሳይሆን፥ ትርጉም ያለው መሆኑን ለማስረዳት ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲጻፉ ምሪትን የሰጠው ይኸው በውስጣችን ያደረው መንፈስ ቅዱስ ነው። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲጻፉ ምሪት የሰጠበትን ሁኔታ መማር ከቻልን፥ ዛሬም መንፈስ ቅዱስ እንዴት በውስጣችን እንደሚሠራ ግንዛቤ ለማግኘት የተመቻቸ ዕድል አለን። ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት በራሳቸው ኀይል አላቸው፤ ሕያዋንና የሚሠሩ ናቸው፤ (ዕብ. 4፥12)። ሐሳባቸውን ከተገነዘብን፥ ትርጉሞቻቸውም እንደዚሁ በሕይወታችን ውስጥ ይሠራሉ።

## የሁሉም ተግባርና ግዴታ

እንግዲህ የመጀመሪያው ተግባራችን ቅዱሳት መጻሕፍትን መረዳት እንጂ ከእነርሱ ትምህርቶችን መፈለግ አይደለም። ብዙ ክርስቲያኖች ከሚያነቧቸው ክፍሎች ሁሉ የተለያዩ ትምህርቶችን የማግኘት ግዴታ እንዳለባቸው፥ ያለዚያ ሙከራቸው ሁሉ ከንቱ እንደ ሆነ፥ መንፈሳውያን እንዳልሆኑም ያስባሉ። ይህን ስሜታቸውን ለማስወገድ ሲሉ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ለየት ያለ «መልእክት» እንዲሰጣቸው ያስገድዱታል። የሚያገኙት ማንኛውም ሐሳብ እነርሱን የሚያረካ ሆኖ ካገኙት መጽሐፍ ቅዱስን ያነበቡበት ጊዜ በከንቱ እንዳልባከነ የቆጥራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ረገድ፥ ይህን የመሰለ ሐሳብ ጤናማ ሳይሆን፥ ያለጥርጥር አክብሮት የጐደለው ነው:: የእኛ ተግባር፥ ራሳችንን ለመጽሐፍ ቅዱስ ማስገዛት እንጂ አንድ ነገር እንዲያደርግልን ማስገደድ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ የእኛ ጌታ ነው እንጂ እኛ የእርሱ ጌቶች አይደለንም:: በአንጻሩም ቃሉ የሚናገረንን መገንዘብ እንጂ ተአምር እንዲሠራልን መሻት የለብንም:: በእያንዳንዱ ጥቅስ ውስጥ ለእኛ የሚሆን መልእክት ባናገኝ ራሳችንን አናስጨንቅ:: የምናነበውን ክፍል የቃሉን ትርጉም ለመገንዘብ ረዘም ላለ ጊዜ ደጋግመን እናንብበው:: ትርጉሙ ሲገባን፥ በሕይወታችንም በተግባር ላይ ውሎ ስንመለከተውና ከዚያ በፊት ለምን እንዳልተገነዘብነው ስናስተውል እንደነቃለን:: አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትርጉሙ ምን እንደ ሆነ ስንገነዘብ፥ በአንጻሩ ከዚህ ክፍል ምን ዐይነት ትምህርት እንደምናተርፍ ራሳችንን መልሰን እንጠይቃለን::

እግዚአብሔር ሕዝቡ መንፈሳዊ ልምምዳቸውን በመንፈስ ብቻ ሳይሆን በአዕምሮም እንዲያደርጉት ይሻል፤ (1ቆሮ. 14፥15):: እርሱ ቃሉ እንዲገባን ይፈልጋል፤ እኛ ቃሉን በምናነብበትና በምናጠናበት ጊዜ እንዲረዳን ብንለምነው ይህን ሊያደርግልን ፈቃዱ እንደ ሆነ እርግጠኞች ነን:: እግዚአብሔር በእምነት ለሚለምኑት የሚሹትን ይሰጣልና፤ (ያዕ. 1፥5)::

በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር የተለያዩ መምህራንን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል፤ ከመካከላቸውም ቅዱስ ቃሉን በበለጠ ለማብራራት በመንፈሱ የታጠቁ ይገኙባቸዋል፤ (1ቆሮ. 12፥8 ፤ ኤፌ. 4፥11-14):: እነዚህ መምህራን በዘመነ ሐዲስ እንደ ነበሩት መምህራን ሁሉ፥ በንግግራቸው ወይም በጽሑፋቸው አማካይነት ያስተምራሉ፤ እኛም የሚናገሩትን ማድመጥና የጻፉትን ማንበብ ይጠበቅብናል::

መምህራን ቅዱሳት መጻሕፍትን ለሌሎች የሚያብራሩ ከሆኑ፥ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጐም በቂና፥ ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል:: ይሁን እንጂ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጐም ማሰብ ያለባቸው መምህራን ብቻ አይደሉም፤ ጉዳዩ ክርስቲያኖችን ሁሉ የሚመለከትና ሊያስቡበት የሚገባ ነው:: ምክንያቱም ሁሉም ክርስቲያኖች የሰሙትንና ያነበቡትን የመመርመር ግዴታ አለባቸው፤ (1ቆሮ. 14፥29 ፤ 1ተሰ. 5፥21 ፤ 1ዮሐ. 4፥1):: ስለዚህ ሁላችንም መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን መገንዘብ፥ ትርጉሙም ምን እንደ ሆነ መረዳትና ማወቅ አለብን::

## *ታማኝነትና ትዕግሥት*

እያንዳንዱ አንባቢ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲያነብ ትርጉማቸውን መገንዘብ ከባድ የሆነበት ጊዜ አጋጥሞት ሊሆን ይችላል:: ይህ ሊሆን የሚችለው በዚያ ዘመን የነበረው ባህልና ቋንቋ፥ ከዛሬው ዘመን ባህልና ቋንቋ እጅግ ርቆ ስለሚገኝ

ነው:: ይሁን እንጂ ስለ መጽሐፍ ቅዱሱ ዓለም- የሚያወሱ መረጃዎች ስላሉ በእነርሱ በመታገዝ ያለ አንዳች ጭንቀት በተነሣሣ መንፈስ እናነባለን፤ እናጠናለን::

በእርግጥ የምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ፥ ለዕለታዊ ሕይወታችን እንዲረዳን እንሻለን፤ ይሁን እንጂ ይህ መሻታችን የጸሓፊውን ሐሳብ በመተርጐም ረገድ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ የለበትም:: በውስጣችን የሚቀሰቀሱ ጥያቄዎችም ሆኑ በጸሎት ጊዜ የምናገኛቸው ሐሳቦች ከትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የመነጩ ላይሆኑ ይችላሉ:: በእያንዳንዱ ጥቅስ ውስጥ የጸሎት መልእክት በመሻት ብናነብ፥ የምንፈልገውን መልእክት ነቅሰን ለማውጣት ስንል በርካታ መሠረታዊ ትረጉሞችን እንዘነጋለን:: ለምሳሌ መዝሙረ ዳዊትን፥ የፊልጵስዩስንና የያዕቆብን መልእክታት ደጋግመን ለማንበብ ስንል መጽሐፈ ነገሥትን፣ ትንቢተ ኤርምያስንና ዕብራውያንን እንዘነጋለን:: በዚሁ ከቀጠልንም መንፈሳዊ ዕድገታችን ይቀጭጫል::

መጽሐፍ ቅዱስ፥ የጸሎት ትምህርቶች፥ የሞራል ሕግጋት ወይም ረቂቅ የሃይማኖት ቀኖና ስብስብ የሆነ መጽሐፍ ሳይሆን በአጻጻፍ ዘይቤ፥ በቅርጽ፥ በስልት፥ በዓላማና በይዘት የተለያዩ ጽሑፎች የሚገኙበት ቅዱስ መጽሐፍ ነው:: ስለዚህ መንፈሳዊ ትምህርቶችን ወይም ለጥያቄዎቻችን መልስ እንዲሰጠን አናስገድደው፤ የማይስማማን ቢሆን እንኳ እያንዳንዱ ጸሓፊ ለመናገር የፈለገውን እንዲናገር እንፍቀድለት:: የጸሓፊውን መልእክት ብናዛባ፥ ለቃሉ ክብር ሰጠነው ማለት አንችልም:: ጥናታችን ዋጋ እንዲኖረው ከፈለግን ታማኝነት አስፈላጊ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ሌላው የሚፈለግብን ነገር ትዕግሥት ነው:: የተጻፈም ይሁን በቃል የተነገረ የቋንቋ ባሕርይ ውስጥ፥ አንድ ሰው ሊናገር የሚችለው በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ብቻ መሆኑን እናስተውል:: በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የተነገረ ሐሳብ ትኩረቱ በአንድ ትምህርት፥ ጸሓፊው በነበረው ሐሳብ ላይ ብቻ ሊሆን ይችላል:: አንድ ጸሓፊ በአንድ ስፍራ የተናገረው ከሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጋር ቢለያይ ሁኔታው ይህን ያህል ሊጋነን አይገባውም:: ደግሞም የአንዱን ክፍል መልእክት ከሌላው ጋር ለማያያዝ እጅግ ለመጠቀም ሰበብ ሊሆን አይችልም::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እምነት የሚሰጠው ትምህርት ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል:: ነቢዩ ዕንባቆም እግዚአብሔር አንዳንድ ነገሮች እንዲሆኑ ለምን እንደ ፈቀደ ለማወቅ ያልተሳካ ምርምር አድርጎ ነበር፤ ነገር ግን ይህን በማድረግ ላይ እያለ፥ በጥበብ ውስጥ እምነትን፥ ኀይልንና ፍቅርን እንዴት እንደሚለማመድ ተማረ፤ (ዕን. 3፥16-19):: የዕንባቆም መጽሐፍ ዓላማው ስላልሆነ ስለ ሌሎች የእምነት ጉዳዮች አልተናገረም፤ ተራራን ስለ ማንቀሳቀስ (ማቴ. 21፥21-22)፥ በሽተኞችን ስለ መፈወስ (ያዕ. 5፥14-15)፥ በክርስቲያኖች አገልግሎት ውስጥ ስጦታዎችን ስለ መለማመድ (1ቆሮ. 12፥7-9) አልተናገረም:: ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች ስለ እምነት በጻፈ ጊዜ አጽንዖት የሰጠው ነገር ኃጢአተኞች

የእግዚአብሔርን ድነት ሊያገኙ የሚችሉት በእምነት መንገድ ብቻ መሆኑን ነበር፤ (ሮሜ 1፥16-17 ፣ 3፥21-22)። የዕብራውያን ጸሐፊ እምነት፥ ጽናትንና ተስፋን እንደሚያካትት ለመግለጽ የተለየ አጽንዖት ሰጠው። እምነት ያላቸው ሰዎች የሚመለከቱት ከሚያዩት ባሻገር ስለ ሆነ ያንኑ በትዕግሥትና በጽናት ይጠባበቃሉ፤ (ዕብ. 11፥1 ፣ 8፥39)። ያዕቆብ ስለ እምነት ሲናገር፥ ሰዎች ልባዊ እምነትካላቸው ያንን በሥራቸው ይገልጹታል ይላል፤ (ያዕ. 2፥18-20)።

እነዚህ ጸሐፊዎች ሁሉ ስለ እምነት ይናገራሉ፤ ሆኖም እያንዳንዳቸው የሚናገሩት በአዕምሯቸው ውስጥ የተለያዩ ጉዳዮችን ይዘው ነው። ጸሐፊዎች ሁሉ አንድ ዐይነት ንግግር ይናገራሉ ብለን መጠበቅ የለብንም፤ በእንጻሩም አንድ የተለየ ጸሐፊ እኛ የምንፈልገውን ርእስ ስላልተናገረ አንቀየመውም። ጸሐፊው እንደ ማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ መናገር የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ በአክብሮት ልናነበው፥ መናገር የሚፈልገውን ሁሉ በራሱ መንገድና በራሱ ጊዜ እንዲናገር ልንፈቅድለት ይገባል።

## ምንባቡ ከሁሉ በላይ ነው

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በምንነጋገርበት ጊዜ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ተነጠለ ስለ አንድ ጥቅስ መናገራችን ሳይሆን ስለ መላው መጽሐፍ ቅዱስ፥ ስለ አንድ ሙሉ መጽሐፍ፥ ስለ አንድ መጽሐፍ ክፍል ነው። ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን እናከብራለን፤ አብዛኛውን ጊዜ የክርስትና እምነታችንን ለመደገፍ ስንል የአንዱን ክፍል ምዕራፍና ቁጥር እንጠቅሳለን። የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን ለማረጋገጥ የምናደርገው ጥረት የሚመሰገን ነው፤ ነገር ግን ይህን እናደርጋለን ስንል የምንባቡን ትርጒም አዛብተን እንዳንገኝ መጠንቀቅ አለብን።

አንዳንድ ጊዜ «ስልታዊ ነገረ መለኮት» የተባለውን እናጠና ይሆናል። ይህ የጥናት መሥመር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተመሠረቱ ርእስ ጉዳዮች ላይ ለማስተማር ከተለያለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶችን አገናኝቶ ያቀርባል። ይሁን እንጂ አስቀድመን ጥቅሶቹ ከተጻፉበት ከመጀመሪያው መቼት በመነሣት ግንዛቤ ሳናገኝ ወደዚህ ዐይነት የጥናት ዘዴ እንዳንገባ መጠንቀቅ አለብን። በአጠቃላይ ከአንዱ መጽሐፍ የተለያዩ ጥቅሶችን አውጣጥተን ከመጥቀሳችን በፊት አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ በሚገባ ማጥናት ይኖርብናል።

እግዚአብሔር የሰጠን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ከሁሉ በላይ ነው። ምንባቡ ከሁሉ በላይ ነው ስንል የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ እንጂ እኛ ልናስቀምጠው በምንሻው መንገድ አይደለም። ስለዚህ አቋማችን የቱንም ያህል ጠቃሚ መስሎ ቢታየንም ምንባቡ ከእኛ አስተምህሮ ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ መሞከር የለብንም። ልክ እንደ ሕይወት ሁሉ፥ መጽሐፍ ቅዱስም፥ ያልተቋጠረና ዝርው የሚመስል፥ አንዱ ከሌላው ፍሰቱን የማይጠብቅ እንዲሁም ያልተመለሱ

ጥያቄዎችን በውስጡ የያዘ ነው:: በመሆኑም አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትርጉሙ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቋሚ ትርጉም ጋር ባይስማማ ትርጉሙን ከማበላሸት ይልቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎማችንን መንገድ መመርመር ተገቢ ነው::

የምናነበው የትኛውም መጽሐፍ ቢሆን፥ በመጀመሪያ የምናገኛቸው ጥቅሶች ግራ ሊያጋቡን ይችላሉ:: አንዳንዶች ለዚህ ችግር መፍትሔ ሳያገኙ አልፈው መሄድ አይፈልጉም:: በምናነበው ክፍል ላይ የተከሠተው የትርጉም ብዥታ አሳሳቢ ካልሆነ፥ ለጊዜው ብናልፈው አይከፋም፤ መጽሐፉን እያጠናን ወደ ፊት ስንሄድ ወይም ወደ ሌላ መጽሐፍ ስንሻገር ያ የትርጉም ችግር ምናልባትም ራሱን በራሱ የሚፈታ ሆኖ ልናገኘው እንችላለን:: ግን ደግሞ ሳይፈታም ይችላል:: ሆኖም አንድ ሌላ ቀን ወደዚህ መጽሐፍ ስንመለስ፥ ቀድሞ ከነበረን መረዳት የበለጠ ግንዛቤ ይዘን ስለምንመጣ፥ ለቀደመው ችግር መፍትሔ እናገኛለን::

የክርስትና ሕይወታችን ሁልጊዜ በለውጥ ሂደት ላይ ነው:: በማንኛውም ደረጃ ቢሆን፥ ፍጹም የሆነ ዕውቀት ሊኖረን አይችልም:: በመሆኑም ችግር ሲገጥመን ትዕግሥተኞች መሆን ይገባናል:: ፈጣን መልስ እንሻ ይሆናል፤ ነገር ግን ሁልጊዜ ፈጣን መልስ አይገኝም::

ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መምጣት ያለብን እንደ ተማሪዎች ሆነን ነው:: ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ስንጀምር ሊታወቅ የሚገባውን ሁሉ ወዲያውኑ ማወቅ እንችላለን ብለን ማሰብ የለብንም፤ በአንጻሩም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለእኛ የሚስማሙንን ጥቅሶች መርጠን በማውጣት እምነታችንን መፈተን አይኖርብንም:: የመጀመሪያው ኀላፊነታችን እግዚአብሔር ሁሉን ለእኛ በሰጠበት ሁኔታ መቀበል ሲሆን ሌላው ደግሞ በምንባቡ መጠቀም ሳይሆን፥ ምንባቡ በእኛ ይጠቀም ዘንድ መፍቀድና መገንዘብ ነው:: ቃሉ አእምሯችንን ሲለውጥ ያኔ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን በጎ ፈቃድ ማወቅ እንችላለን፤ (ሮሜ 12፥2)::

## ፪

### በማስተዋል ማንበብ (1)

#### ከመጀመራችን በፊት

ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጐም ሥርዐትና ዘዴ በምንነጋገርበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ተከታታይ ጽሑፍ ካለመሆኑም በላይ፥ በዘይቤውና በይዘቱም ከዳር እስከ ዳር ወጥ ያልሆነና በቅርጻቸውም በጣም የተለያዩ መጻሕፍት ስብስብ ስለ ሆነ ነው። ስለዚህ ልዩ ልዩ የሆኑትን፥ እነዚህን መጻሕፍት በተለያዩ መንገዶች ማንበብ ይኖርብናል። ይሁንና ለየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ጥናት መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮች አሉ።

የትናንቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓለም ከዛሬው ይለያል። ብዙ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነቡበት ጊዜ ይህን ሐቅ ይረሳሉ። መጽሐፍ ቅዱስን በተሻለ ሁኔታ መገንዘብ ከፈለግን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ዓለም መልክዐ ምድር፥ ማኅበረ ሰብና ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ዕውቀት ሊኖረን ያስፈልጋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ዓለም ተብሎ የሚጠራውን አካባቢና በታሪክም የሚጠቀሰውን ስፍራ ሁሉ በተመለከተ መረጃዎችን ከመዝገበ ቃላት፥ ዐውደ ጥበብ፥ አትላስ፥ ማጣቀሻ መጽሔት ወይም ፊልም ልናገኝ እንችላን። ከፍተኛ የመማር ፍላጎት ካለን ካሰብነው በላይ፥ ዕውቀታችንን ሊያዳብሩ የሚችሉ ብዙ ዕድሎችን እናገኛለን።

#### አገሩን ማወቅ

እዚሁ በአገራችን ውስጥ ወዳሉ ወደ ሌሎች ስፍራዎች ስላደረግነው ጉዞ በአቅራቢያችን ለሚኖሩ ወዳጆቻችን ብናጫውታቸው ስለነዚያ ቦታዎች ብዙ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይችላል። እነዚህ ስፍራዎች የሚገኙት በሰሜን ወይም በደቡብ መሆኑን፥ የአየር ጠባያቸው ሞቃት ወይም ብርዳማ፥ ደረቃማ ወይም ዝናባማ የቦታዎቹ አቀማመጥ ጠፍጣፋ ሜዳ ወይም ተራራማ እንደ ሆኑ ያውቃሉ። ይህን ማወቃቸውም ትረካችን እንዲስባቸው ያደርጋቸዋል። ነገር ግን ወደ አንድ ሩቅ አገር ስላደረግነው ጉዞና ስለማያውቋቸው ስፍራዎችና ስሞች ብንዘረዝርላቸው፥ ባለፈው ታሪክ ላይ የነበራቸው ስሜት ዐይነት አሁን አይኖራቸውም። ለአብዛኛው ታሪካችን ትኩረት ሊሰጡትና የትረካችንን ዋና ክፍል ሊያገኙት አይችሉም።

ይህንን ሁለተኛውን ክስተት ያነሣንበት ምክንያት፥ ብዙዎቻችን መጽሐፍ ቅዱስን የምናነብበት መንገድ አሳዛኝ ምሳሌ በመሆኑ ነው። ብዙ ጊዜ ለቦታ ስሞች ትኩረት አንሰጥም፤ ምናልባትም የስሞቹ አነባበብ ከብዶብን ወይም የሚገኙበትን

ስፍራ ፈልገን ለማግኘት ሰንፈን ይሆናል፤ ከዚህ የተነሣ ጸሐፊው የደከመባቸውን ጠቃሚ ዝርዝር ነጥቦች አግኝተን ሳናውቃቸው እንቀራለን::

በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕራፍ 17 እና 18 ላይ የተጠቀሱት ቦታዎች የት እንደሚገኙ ካላወቅን በስተቀር÷ ታሪኩ ረጅም÷ ትርጉሙ ትንሽ ሆኖ እናገኘዋለን:: የታሪኩ ዓላማ ከዳን ጐሳ የሆኑ ሰዎች÷ ከጐሳቸው ምድር ከሜድትራንያን ባሕር ዳርቻ በኀይል እንዲነሡ ተደርገው ከእስራኤል በስተሰሜን ርቆ በሚገኝ አዲስ አካባቢ እንዴት እንደ ሠፈሩ የሚያወሳ ነው:: በአዲስ ኪዳን የጳውሎስን የወንጌል ተልእኮ ጉዞ በአትላስ ካልተከታተልነው በስተቀር÷ የተልእኮውን እውነተኛ ትርጉም እናልፈዋለን:: ጳውሎስ ወዴት እንደ ሄደ ስናስተውል ግን ከተግባሮቹ በስተጀርባ ግልጽ የሆነ ስልት ማጤን እንችላለን::

አገሮቹና ከተሞቹ ያሉባቸውን ስፍራዎች ከማወቃችን በላይ ÷ ምድሩም ምን ዐይነት ምድር እንደ ሆነ ማወቅ ይኖርብናል:: ለምሳሌ:- በአሁኑ ጊዜ ሳይቤሪያ ስለሚባለው አገር ሲወሳ ይህ አገር እጅግ ብርዳማና በበረዶ የተሸፈነ ምድር መሆኑ÷ በአንጻሩ ደግሞ ሰኻራ የተባለ ስፍራ ስም ሲጠራ ይህ ስፍራ እጅግ በጣም ሞቃታማ መሆኑ ትዝ ይለናል:: ስለ ሱዊዝ ባሕረ ሰላጤ ስንሰማ÷ ይህ ባሕረ ሰላጤ ከሜዲትራንያን ባሕር ወደ ሕንድ ውቅያኖስ ለመርከቦች ጉዞ አቋራጭ መሥመር መሆኑን እናስባለን:: በዚህ ሁኔታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምድር ጋር ዝምድና ያላቸውን አገሮች ለማወቅ የሚያግዘንን ዕውቀት እናዳብራለን::

ለምሳሌ ኤዶም የሚባለው መሬት ጠፍ÷ ደረቅና ዐለታማ ተራራዎች የሚገኙበት ስፍራ ነበር፤ ይህ ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለዚህ ምድር የተሰጠውን ማስረጃ ለመገንዘብ ይረዳናል፤ (ዘዳ. 2÷1-3 ፤ ኤር. 49÷16-17፣ ሕዝ. 35÷7-8):: ምንም እንኳን ይህ ምድር ለእርሻ አመቺ ባይሆንም በቀይ ባሕር ዳር ይገኝ በነበረውና ዔጽዮንጋብር ወይም ኤላት በተባለው ወደቡ ከዓለም የንግድ ልውውጥ ጋር ግንኙነት ነበረው:: ይህም ኤዶማውያን ከግብርና ይልቅ ነጋዴዎች የሆኑበትን÷ ዔጽዮንጋብርን ለመቈጣጠር ይፈልጉ በነበሩ ጐረቤቶቻቸውና በእነርሱ መካከል ግጭት የተነሣበትን ምክንያት ያስረዳል፤ (ዘዳ. 2÷8 ፤ 1ነገ. 9÷26-28 ፤ 22÷48 ፤ 2ነገ. 14÷22 ፤ 16÷6፤ አሞጽ 1÷6ና9)::

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ስለ ኤዶም ምድር ዝርዝር ነገር ማቅረብ አላስፈለጋቸውም ነበር፤ ምክንያቱም ልክ እኛ ዛሬ ስለ ሰኻራ ምድረ በዳ ወይም ስለ ሱዊዝ ባሕረ ሰላጤ ደኅና አድርገን እንደምናውቅ ሁሉ÷ አንባቢዎቻቸውም ስለ ኤዶም ምድር በሚገባ ያውቁ ስለ ነበረ ነው:: እኛ ግን ስለ ኤዶም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምናነብበት ጊዜ÷ በእኛና በኤዶም ዘመን መካከል በጊዜ ርቀት ተለያይተን እንገኛለን:: ሆኖም ስለ ኤዶም የነበረውን ሁኔታ ለማወቅ ጥረት ማድረግ አለብን፤ ያለዚያ ጸሐፊው ስለዚህ ስፍራ ያሰፈረውን ዋና ቁምነገር ሳናውቅ እንቀራለን::

ከኤዶም አገር ይልቅ ይበልጥ ትኩረት የሚሰጣት የኢየሩሳሌም ከተማ ናት:: ኢየሩሳሌም ጠንካራ ቅጥር ያላትና በተራራ ላይ የተመሠረተች ከተማ መሆኗን ባናውቅ ኖሮ፥ ዳዊት ይህችን ከተማ በድል ስለ መያዙ በ2ኛ ሳሙኤል በምዕራፍ 5 ላይ የተጻፈው ማስረጃ ትርጉም ባልሰጠንና በዳዊት መዝሙራት ውስጥ ስለ ኢየሩሳሌም የተጻፈው ማስረጃም ከግንዛቤችን ውስጥ ባልገባ ነበር::

በተመሳሳይ ሁኔታ፥ የዮርዳኖስ ወንዝ በብዙ ታሪኮች ውስጥ በምን ምክንያት እንደ ተጠቀሰ ለመገንዘብ፥ የወንዙን እውነኛ ሁኔታ አስቀድመን ማወቅ ይኖርብናል:: ወንዙ ጥቅጥቅ ባለ ደን የተከበበ፥ ቀጥ ያለ የባሕር ጠረፍ ነበረው፥ በጥልቅ ሸለቆ ውስጥ የሚፈስ ነበር፤ ይህ ሁኔታ ወንዙን ለመሻገር አስቸጋሪ አደረገው:: መሻገር የሚቻለው በጥቂት ስፍራዎች ብቻ ነበር፤ (ኢያ. 2፥7 ፤ መሳ. 3፥28፤ 7፥24፤ 12፥5):: ወንዙ የእስራኤልን ምድር በምሥራቅና በምዕራብ ይከፍለዋል፤ ጸሐፊው «ከዮርዳኖስ ማዶ» ሲል የትኛውን አቅጣጫ እንደሚናገር ማወቅ አለብን፤ (ዘኍ. 32፥5 ፤ ኢያ. 22፥4 ፤ 2ሳሙ. 19፥15 ፤ ዮሐ. 10፥40)::

ስለ ዮርዳኖስ ወንዝ፥ ኤዶምንና ኢየሩሳሌምን በማወቃችን የምናገኘው ጥቅም ግልጽ ነው:: ይሁን እንጂ እነዚህ ስፍራዎች የተጠቀሱት እንደ ምሳሌ ብቻ ናቸው:: እነዚህ ስፍራዎች የሚሰጡን ጥቅሞ እጥፍ ድርብ የሚሆኑት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጠቀሱት ሌሎች አገሮች፥ ከተሞች፥ ተራራዎች፥ ወንዞችና ሸለቆዎች በምናጠናበት ጊዜ ነው:: እንዲህ ማለት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ከማጥናታችን በፊት፥ በአትላስ ላይ ያሉ ስፍራዎችን ወይም መልክዐ ምድር በቃል ማጥናት አለብን ማለት አይደለም:: ይህ ሐሳብ የቀረበው፥ መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ ንባባችንን ቆም አድርገን የሚያጋጥሙንን ስፍራዎች የት እንደሚገኙና እንዴት እንደ ሆኑ አጥንተን እየተገነዘብን እንሄዳለን ለማለት ነው:: ይህን ቅድመ ሁኔታ ካሟቻችን ለሚቀጥለው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባችን የሚያዘጋጀንን ጠቅላላ ዕውቀት እናከማቻለን:: በአንድ ታሪክ ውስጥ የአንድን ስፍራ ምንነትና ጠቃሚነት ካወቅን፥ ይህ ስፍራ በሌላ ታሪክ ውስጥ ቢገጥመን ልንረሳው አንችልም::

## የሕይወት መንገድ

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ፥ በእርግጠኝነት ከጥንቱ ዓለም ሕይወት የዕውቀትን ጥቅም እናተርፋለን:: ይህ እንግዲህ ከአንድ ባህላዊ ወግና የሃይማኖት ሥርዐት የሚያልፍ ዕውቀት ነው:: ይህ ሁኔታ በአስተሳሰባችን ላይ ለውጥን ያስከትላል:: እነዚያ የጥንት ሰዎች ወደ ነበሩበት ገጽታ ይወስደንና ነገሮች ምን ትርጉም እንደሚሰጧቸው ተሰምቶን እንድንገነዘባቸው ያደርገናል::

ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላሉ አንዳንድ ታሪኮች ማወቅ ከፈለግን ወደ ኋላ መለስ ብለን በዘመነ ብሉይ ስለነበሩት ልማዳዊ የእስራኤላውያን

የግብርና ልምዶች (ስለ ማረስ፥ መዝራት፥ ማጨድና ማበራየት) መገንዘብ አለብን:: አንዳንድ ጊዜ ስለ እስራኤላውያን ሃይማኖታዊ በዓላት ለመገንዘብ ዓመታዊውን የግብርና ዑደት ማወቅ እንዳለብን አንረዳም:: የእነርሱን ሃይማኖታዊ ሥርዐቶች ትርጉም ባናውቅ፥ ሥርዐቶቻቸው ምን ያህል ከሕዝቡ ዕለታዊ ሕይወት ጋር እንደተሳሠሩ ሳናስተውል እንቀራለን::

በእስራኤላውያን የግብርና ሕይወት ውስጥ ጉጂ የሆኑ ልምዶችም ነበሩ:: ከእነዚህም መካከል ለበኣል የመስገድ ሁኔታ ይገኝበታል:: ይህ ችግር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተደጋግሞ ታይቷል፤ ታዲያ የዛሬዎቹ አንባብያን ይህ ሁኔታ እንዴት በተግባር ላይ እንደሚገለጥ ካልተረዱት በስተቀር ችግሩን ማስተዋል ያዳግታቸዋል:: አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ ቆም ብሎ «አሁን ስለ በኣል እነግራችኋለሁ» አይልም፤ ምክንያቱም ታሪኩን የጻፈላቸው ሰዎች ስለበኣል ማንነትና ሁኔታ ደኅና አድርገው ያውቃሉና ነው:: ነገር ግን ይህንኑ ታሪክ ከጥቂት ሺህ ዓመታት በኋላ በምናነብበት ጊዜ ስለ ጥንቱ ታሪክና ስለ አተገባበሩ መመርመርና ማጥናት ይኖርብናል::

ስለዚህ ነገር መረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ወይም ዐውደ ጥበብ ውስጥ ብናገኝም ምንጩ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: እነዚህ መረጃዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዝርው ሆነው በየስፍራው ይገኙ ይሆናል፤ እኛ ግን የምንፈልገውን መረጃ አሰባስቦ የያዘ መጽሐፍ ፈልገን በማጥናት ጊዜያችንን ከብክነት ማዳን እንችላለን:: የበኣልን አምልኮት በተመለከተ፥ ከአንድ መጽሐፍ የምናገኘው ማብራሪያ በሥራው ሊጠቅመን ይችላል፤ ምክንያቱም በኣልን የማምለክ ሥርዐት ቀድሞውንም ቢሆን የብሉይ ኪዳን ነቢያትን በአያሌው ያሳሰባቸው ችግር ነበር::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የነበረው ስብከት፥ ልክ እንደዛሬው ስብከት፥ ትኩረት የሚሰጠው ስለ አካባቢ ችግሮች ሳይሆን፥ በአካባቢ ልምዶችና ባህሎች ላይ የተመሠረቱ ማብራሪያዎችን በመጠቀም ላይ ነበር:: ስለጥንት ሰባክያን ግንዛቤ እንዲኖረን ከፈለግን ተመሳሳይ ልምዶችንና ባህሎችን ለማወቅ የጥናት ጊዜ እንዲኖረን ማድረግ አለብን::

ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ አዲስ ኪዳንን ስናነብ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ልጅ ተቀባይነትን አግኝቶ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባል ስለመሆን ያስተማረውን ትምህርት ለመገንዘብ ያስቸግረናል፤ ምክንያቱም በሌላ ስፍራ፥ «እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ» ከሚለው ጋር የሚቃረን ስለሚመስል ነው:: ነገር ግን እነዚህ ስለ ድነት የተለያዩ አገላለጾች፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምናገኛቸው ከብዙዎቹ ሁለቱ ናቸው:: ሥዕሎች አንድን ርእሰ ጉዳይ በተለያዩ ገጽታዎች ለማሳየት ይጠቅማሉ:: በዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ የነበረውን የልጅነት ሁኔታ ስንገነዘብ፥ ጳውሎስ ለመግለጽ የፈለገውን እውነት በአድናቆት እንቀበላለን:: የጥንት ልማዶችን ማወቃችን፥ ክርስቲያናዊ አስተምህሮን እንድንገነዘብ ይረዳናል::

## መቼ? እንዴት? ለምን?

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መልክዐ ምድር፥ ባህልና ሃይማኖቶት ከማወቃችን በተጨማሪ ስለ ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት፥ ታሪካዊ መቼት መረዳት አለብን:: አብዛኛውን ጊዜ ስለ ብሉይ ኪዳን ነቢያትና ስለ አዲስ ኪዳን መልእክቶች ማወቅ የምንችለው መቼ፥ የት፥ በምን ዐይነት ሁኔታና ለምን ዓላማ እንደ ተጻፉ ስንገነዘብ ነው:: ስለ ነቢያት ለማወቅ መጻሕፍተ ነገሥት መሠረት እንደ ሆኑ ሁሉ፥ ስለ ጳውሎስ መልእክቶች ለማወቅም የሐዋርያት ሥራ መሠረት ነው::

አንዳንድ መጻሕፍት ገና ከመጀመሪያቸው ላይ ስለምን ርእስ ወይም ስለምን ዓላማ እንደሚናገሩ ይጽፋሉ:: ሚክያስ በራሱ መጽሐፍ፥ በተለይ ስለ ሰማርያና ስለ ኢየሩሳሌም ኀጢአት እንደሚናገር ይጠቅስና ስለ ጻፈበት ዘመንም ለይቶ ያሳውቃል፤ (ሚክ. 1፥1-5):: ሐዋርያው ጳውሎስም ለገላትያ ክርስቲያኖች መልእክቱን ሲጽፍ፥ ከእውነተኛው እምነት ወደ ሐሰተኛ ትምህርት ያዞራቸውን በመግለጽ ይጽፋል፤ (ገላ. 1፥6-9)::

ግን ሁሉም ጸሐፊዎች ለመጻፍ የተነሣሡበትን ምክንያት አያብራሩም፤ ስለዚህ የጽሑፋቸውን ጭብጥ ለመረዳት ጊዜ ወስደን መመርመርና ማጥናት ይኖርብናል:: ከእኛ በፊት የነበሩ ሰዎችም ይህን የመሰለ ተግባር ፈጽመዋል፤ እነዚህ ሰዎች በምርምርና በጥናታቸው አማካይነት ያቀረቧቸውን ሥራዎች ማግኘ ት ከቻልን ለማመሳከር ማመንታት የለብንም:: ምናልባትም በጻፏቸው ሐሳቦች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ላንስማማ እንችላለን፤ ሆኖም ከጽሑፋቸው ውስጥ ቢያንስ ሐሳባችንን የሚቀሰቅሱ ጠቃሚ መረጃዎች ልናገኝ እንችላለን::

ብዙ ጊዜ ከአንድ ጥናታዊ ሥራ የምንፈልገው ለምናጠናው መጽሐፍ ፍንጭ እንዲሰጠን ነው:: ለምሳሌ:- ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ለመገሠጽ ሲጀምር፥ «በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ከቀሎዔ ቤተ ሰብ ስምቻለሁና» (1ቆሮ. 1፥11) ከሚለው ሐሳቡ በቆሮንቶስ ስለ ነበረው ሁኔታና ከዚያም ይህ መልእክት የተጻፈበትን ዓላማ እንገነዘባለን:: «በመካከላችሁ የዝሙት ርኩሰት እንዳለ በእርግጥ ይወራል» ብሎ ሲናገር (1ቆሮ. 5፥1) ይህን መልእክት ሲጽፍ የተነሣሣበትን ምክንያት በመጠኑም ቢሆን ልንረዳ እንችላለን:: እንዲሁም በ1ቆሮ. 7፥1) ላይ «ስለጻፋችሁልኝስ ነገር» ብሎ ሲያክልበት ከዚህ ሁኔታ የቆሮንቶስ ሰዎች በርካታ ጥያቄዎችን መዝግበው እንደላኩለትና እርሱም ጥያቄዎቻቸውን አንድ ባንድ ተመልክቶ መልስ እንደሰጠ እንገነዘባለን፤ (ለምሳሌ:- 1ቆሮ. 8፥1 ፤ 12፥1 ፤ 16፥1):: መልእክቱ የጽሑፉን መነሻ እንድናብራራ የሚረዱ መግለጫዎችን፥ እነዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ በምን ምክንያት እንደ ጻፈ፥ በዚያን ጊዜ የት እንደ ነበረ፥ ማን ከእርሱ ጋር እንደ ነበረ እንዲሁም ዕቅዱ ምን እንደ ሆነ ወዘተ... ይሏል::

## ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ዐይነቶች

አብዛኛውን ጊዜ አንባቢዎች መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች እንዳሉት ይዘነጋሉ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተራኪ ሥነ ግጥሞች፥ ጥበባዊ አባባሎችና ሕጎች፥ ራእዮችና ደብዳቤዎች፥ ክርክሮችና የዘር አወራረድ ሐረጎች ይገኙበታል:: መጻሕፍቱ፥ አንዱ ከሌላው በጣም ይለያል:: በአንዱ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ክፍሎች እንኳ የተለያዩ ዘይቤዎች ስላሏቸው የምናነበው መጽሐፍ ምንም ይሁን ምን ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጹን ማወቅና በዚያው መሠረት መተርጐም ይገባናል::

ሌሎች ሥነ ጽሑፎችን ስናነብ ለነገሩ የምንሰጠውን ትኩረት መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ይህን ሚዛናዊ ፍርድ መስጠት ይሳነናል:: ቀጥተኛ ታሪክ ከግጥም የተለየ መሆኑን ስለምናውቅ፥ በተለየ ስልት እናነበዋለን:: ጋዜጣ በምናነብበት ጊዜ በዜና ዘገባዎች፥ በማስታወቂያዎች፥ በርእሰ አንቀጾች፥ በጋዜጦች ላይ ስለሚገኙ ስለ ታወቁ ሰዎችና ስለ ጊዜው ሁኔታ በጊስ መልክ በሚናገሩ ሥዕሎች መካከል ያለውን ልዩነት እንገነዘባለን:: ከአንዱ የሥነ ጽሑፍ ዐይነት ወደ ሌላው በምናልፍበት ጊዜ የማንበብ ስሜታችንን ወዲያውኑ እናስተካክላለን፤ ጸሐፍያኑም ቢሆኑ ይህን የመሰለ ማስተካከል እንድናደርግ ይጠብቁብናል:: ይህን ካላደረግን ሐሳባቸው ሳይገባን ይቀርና ስሕተት ላይ እንወድቃለን::

የተለያዩ የቀድሞዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች፥ ጸሐፊዎች የተለያዩ መልእክቶችን በተለያዩ መንገዶች እንደሚያቀርቡ በግልጽ ተገንዝበው ነበር:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ካህናት፥ ነቢያትና የጥበብ መምህራን ነበሩ፤ (ኤር. 18፥18):: በአዲስ ኪዳን ዘመንም ወንጌላውያን ፥ ካህናትና መምህራን ነበሩ፤ (ኤፌ. 4፥11):: ሁሉም የተለያዩ ተግባራት የነበሯቸው ሲሆን፥ እነዚህን ተግባራት በተለያዩ መንገዶች ይፈጽሙ ነበር::

ለምሳሌ:- በሙሴ ሕግ ሥርዐትና በነቢያት ጽሑፎች መካከል የነበረውን ልዩነት አስቡ:: ነቢያቱ ብዙ ጊዜ የመሥዋዕት ሥርዓቶችን ያወግዙ ነበር፤ ነገር ግን ይህን የሚያደርጉት የሙሴን ሕግ ስለሚቃወሙ አልነበረም:: እነርሱ ይቃወሙ የነበሩት የመሥዋዕቱን ሥርዐት ያከናውኑ የነበሩትን ሰዎች ድርጊት ነበር:: የሕጉ ሥነ ጽሑፍ፥ ሕዝቡ ሊጠብቋቸው ቃል ኪዳን የገቡላቸውን ግዴታዎች ነቅሶ በማውጣት ማስገንዘብ ሲሆን የካህናቱ ተግባርም ይህን ማስተማር ነበር:: ነቢያዊው ሥነ ጽሑፍ ግን የተጻፈው ከተለየ የአስተሳሰብና አቅጣጫ ነበር:: ነቢዩ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ችግር እንዳለ በእግዚአብሔር ዐይን ይመለከታል፤ መልእክትም ከእግዚአብሔር ወደ ሰዎች ያመጣል:: ነቢይ ሰባኪ እንጂ ሕግን ሰጪ አይደለም፤ ኀጢአተኞች ኀጢአታቸውን ትተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ይነግራቸዋል፤ ይህን ከአላደረጉ ግን በኀጢአታቸው ውጤት እንደሚሰቃዩ ያስጠነቅቃቸዋል::

የጥበብ መምህር አድማጮቹ እንደ ሕግ ሰጪ ወይም እንደ ነቢይ እንዲቈጥሩት አይፈልግም። (እንደ ኢዮብ፥ ምሳሌና መክብብ ያሉ ቅዱሳት መጻሕፍት የጥበብ መምህር ጽሑፎች ናቸው)። የጥበብ መምህር፥ እንደ ነቢይ እግዚአብሔር ከተናገረው ነጥብ ተነሥቶ «ጌታ እንዲህ ይላል» በማለት ሐሳቡን አይገልጽም። የሕይወትን ችግሮች ከተራ ሰው አንጻር ተነሥቶ ይመለከታል። ምንም እንኳ ሁልጊዜ እንደ እምነት ሰው ሆኖ ቢጽፍም አቋሙ ይኸው ነው። ዋናው ጉዳይ፥ ነቢዩና የጥበብ መምህሩ ሰዎች መልእክቶቻቸውን በተለያዩ መንገዶች እንዲመለከቷቸው ይጠብቃሉ። የነቢያትን መጽሐፍ በምንተረጕምበት መንገድ የጥበብ መጽሐፍን መተርጐም አይገባንም። የጸሐፍያኑን አቋም መረዳት ከተሳነን የሚናገሩትንም መገንዘብ አንችልም።

## ልዩ ምክንያት

በሕዝቅኤል፥ በዘካርያስና በራእይ ውስጥ የምናገኛቸው፥ ስለ ዓለም ፍጻሜ የሚናገሩ አቡቀለምሲሳዊ ጽሑፎች ልዩ የሆነ አተረጓጐምን ይሻሉ። ስለ አስፈሪ እንስሳት፥ መልክና ምሥጢራዊ ቊጥሮች ይገልጻሉ። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርና ሕዝቡ በድል የሚወጡትን ግጭት ወይም ጦርነት ያሳያሉ።

አቡቀለምሲሳዊ ጽሑፍ ጸሐፊዎች በነበሩበት ዘመን የነበሩ ሰዎች ይህን ከመሰለ ሥነ ጽሑፍ ጋር ይተዋወቃሉ፤ የራእዮችንም ምልክቶች (ትምህርቶች) እንዴት እንደሚተረጕሟቸው ያውቃሉ። ዛሬ እኛ እነዚህን የመሰሉ ጽሑፎች ቶሎ መገንዘብ አንችልም፤ ምልክቶቹንም ቃል በቃል ብንተረጕማቸው የጸሐፊውን ሐሳብ ወይም ትርጕም እንስታለን።

አቡቀለምሲሳዊ ጽሑፎች ምን እንደ ሆኑ ማወቅ እንፈልጋለን፤ ነገር ግን ጸሐፊዎቹ አብዛኛውን ጊዜ ዛሬ እኛን ስለሚያስጨንቁን ነገሮች ምንም ማለት ወይም መናገር አለመፈለጋቸውን ማስተዋል አለብን። እኛ ማወቅ የሚያስፈልገንን ባይናገሩ እዚሁ ላይ ልንተዋቸው ይገባል። እኛን እንዲስማሙ ለማድረግ ብለን ቃሎቻቸውን ልናጣምምባቸው አይገባም። በነዚያ በአስቸጋሪ ጊዜያት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ምን እንዳደረገ ስናውቅ፥ ምናልባት ከጽሑፎቻቸው ውስጥ ትምህርት እናገኛለን፤ በዚህም እግዚአብሔር ዛሬ ከእኛ ጋር ምን እየሠራ እንደ ሆነ ራሳችን እንማራለን።